# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

አቅራቢዎች



## የእሳት ሰው::

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Lazarus, Alastair Paterson

ያሻሻለው (አሻሻሎ የጻፈው): E. Frischbutter

የተተረጎመው: Zemendale Translation Service
email: zemendale@gmail.com
Po Box 32155, Addis Ababa, Ethiopia

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2022 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

በእስራኤል ሁሉም ነገር መጥፎ ይመስላል፡፡ ንጉሱና ንግስቲቱ እግዚአብሔርን ይጠሉታል፡፡ እንዴት ያለ መጥፎ ምሳሌ ነው! በፍጥነትም ሰዎቹ እግዚአብሔርን ጠልተው ጣኦታትን ማምለክ ጀመሩ፡፡ እግዚአብሔርን የሚወድ አለ?



አዎ! ጥቂት የሆኑ ታማኝ አምላኪዎቹ ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ፣
ከእነርሱ አንዱ የሆነውን ያዋራ ነበረ ፤ ኤልያስን ፡፡



ኤልያስም ክፉ የሆነውን ንጉስ
አክዓብን ነገረው ፤ “ሕያው
አምላክ እግዚአብሔር እንደሚል
፤ከእኔ ቃል በቀር በእነዚህ
አመታት ዝናብም ሆነ ጠል
በእስራኤል ላይ አይሆንም።”
ይሔም ማለት ረሐብ
ነው ። እግዚአብሔር
ሕዝቡን እስራኤልን
በክፋታቸው እንዲቀጥሉ
አልፈቀደም።





ንጉሡን

ካስጠነቀቀው በኋላ፣ እግዚአብሔር ኤልያስን በምድሪቱ ባለ ጸጥ ወዳለ ስፍራ መራው፡፡ እዚያም፣ በምንጭ አጠገብ ፣ ኤልያስ ጠበቀው፡፡ እግዚአብሔርም ቁራዎችን እንዲመግቡት ላካቸው፡፡ እነርሱም በምሽትና በጠዋት ዳቦ እና ሥጋን ያመጡለት ነበረ፡፡ ኤልያስም ከምንጩ ይጠጣ ነበረ፡፡



ምንጩም
በፍጥነት ደረቀ ፤
ምክንያቱም
በምድሪቱ ላይ
ምንም አይነት ዝናብ አልነበረም። የእግዚአብሔር ቃል እውነት እየሆነ ነበረ። ምድሪቱ ሁሉ በውኃ ድርቅ ውስጥ ነበረች። አዝዕርቱም አያድጉም ነበረ። ሰዎችም ይራቡ ነበረ። ምንአልባት ኤልያስም ውኃው በመድረቁ የተነሳ በእርሱ ሕይወት ምን እንደሚሆን ለማወቅ ጓግቶ ነበረ።

እግዚአብሔርም ለኤልያስ እንዲህ አለው ፣ “ተነስና ወደ ሰራፕታ ሂድ ፤ በዚያም ሁን። እይ ፣ አንተን እንድትመግብህ አንዲትን መበለት አዛታለሁ።” እግዚአብሔር የአገልጋዩን ፍላጎት ያውቅ ነበረ። ነገር ግን እርሱን ለመመገብ ይሔ እንዴት ያለ እንግዳ መንገድ ነው;

በተዋረደ መልኩ ፣ ኤልያስ



እግዚአብሔርን ታዘዘው። ወደ ሰራፕታም ሲገባ ፤ መበለቲቱ በከተማው መግቢያ ላይ ለእሳት የሚሆን እንጨትን እየሰበሰበች ነበረ።

ኤልያስም ሴቲቱን እንዲህ
ብሎ ጠየቃት፣ “እባክሽን ትንሽ
ውኃ በኩባያ አድርገሽ
አምጪልኝ፡፡” “ዳቦ የለኝም፡፡”
መበለቲቱም መለሰች፡፡
“ትንሽ ዱቄት እና በማሰሮ
ያለ ትንሽ ዘይት ነው፡፡”



በሚያሳዝን ሁኔታ ፣
ሴቲቱ ለነብዩ ይሔ
ሲያልቅ እርሷና ልጇ
እስከሞት ድረስ
ይራቡ ነበረ፡፡

ኤልያስም አለ ፣ “አትፍሪ ፣ ከእርሱ ለእኔ የሚሆን ትንሽ ዳቦ ስሪልኝ ፤ ከዚያም ለአንቺና ለልጅሽ ስሪ።” “እግዚአብሔር ዝናብን በምድሪቱ ላይ እስኪያዝዝ ድረስ ፣ ዱቄቱንም ሆነ ዘይቱን አንጠቀመውም።” ያ እንዲሆን እግዚአብሔር ታዓምራትን ማድረግ አለበት። እርሱም አደረገ! ሴቲቱና ልጁ ለብዙ ዘመናት በሉት ፣ ነገር ግን ዱቄቱም ሆነ በማድጋ ያለው ዘይት አላለቀም ነበረ።





ኤልያስም ከእነርሱ ጋ ኖረ
፡፡ አንድ ቀን አሳዛኝ ነገር
ተከሰተ፡፡ የባልቴቷ ልጅ
ሞተ፡፡ ኤልያስም
የሞተውን ልጅ አካል
ወደ ሰገነት ይዞ ወጣ፡፡
ወደ እግዚአብሔርም
እንዲህ ሲል ጮኸ ፤" ኦ!
እግዚአብሔር አምላኬ
እጸልያለሁ ፤ የዚህ ልጅ
ነፍስ ትመለስ፡፡"
እንዴት ያለ ሊሆን
የማይችል ጸሎት ነው!

እግዚአብሔርም የኤልያስን ድምጽ ሰማና ፣ የልጁ ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች ፤ እርሱም ተነቃቃ፡፡ ኤልያስም ልጁን ይዞ ለእናቲቱ ሲሰጣት ፣ እርሷ እንዲህ አለች ፣"በአፍህ ያለው የእግዚአብሔር ቃል እውነት እነደሆነ በዚህ አወቅሁ፡፡"



ከሶስት ዓመታት በኋላ ፣ እግዚአብሔር ኤልያስን ወደ ንጉሱ መልሶ ላከው፡፡
እንዲህም አለ ፣"በምድሪቱ ላይ ዝናብን እልካለሁ፡፡" ወደ አክዓብ ሲሔድ ፣
ኤልዛቤል አንድ መቶ የሚሆኑ የእግዚአብሔር ነብያትን ገድላቸው ነበረ፡፡
ነገር ግን ኤልያስ አልተከራከረም ፤



ሁለቱ ሰዎች ሲገናኙ ፣ ኤልያስ
አክዓብን ስምንት መቶ ሃምሳ
የሚሆኑትን ሐሰተኛ ነብያትና
የእስራኤልን ሕዝብ
እንዲሰበስብ ተገዳደረው።
ቀርሜሎስ በሚባለ ተራራ
ላይም ፣ ኤልያስ ለሰዎቹ
እንዲህ አለ ፣"እግዚአብሔር
አምላክ ከሆነ ፣ ተከተሉት።"



ኤልያስም ለመስዋዕት የተዘጋጁ ሁለት በሬዎች ነበሩት ፤ ነገር ግን እነርሱን ለማቃጠል ምንም አይነት እሳት አልተዘጋጀም። እርሱም እንዲህ አለ ፣ “የአማልክቶቻችሁን ስም ጥሩ ፤ እኔም የጌታን ስም እጠራለሁ።” “በእሳት የሚመልሰው እርሱ ፣ እግዚአብሔር ነው።” ሕዝቡም ፣”ይሔ ትክክል ነው።” አሉ።



ከጠዋት ጀምሮ እስከ ምሽት ድረስ ሐሰተኛ ነብያቱ ሐሰተኛ የሆኑ አማልክቱን መጥራት ጀመሩ:: እየዘለሉና እየደነሱ ፤ እስኪደሙ ድረስ በስለት ሰውነታቸውንም ይቧጭራሉ ፤ ነገር ግን አንዲትም እሳት አልወረደችም::





ኤልያስም እንጨቱን
ረበረበውና ፣ በውኃ
መስዋዕትን ሰራ ፤ ጸለየም ፣
"እግዚአብሔር ሆይ ፣ አንተ
ጌታ አምላክ ነህ ፤......"
ከዚያም የእግዚአብሔር
እሳት ወረደ። በሬዎቹንና
እንጨቱንም በላቸው ፤
ከዚያም ድንጋያማውን
መሰዊያም አቃጠለው።

ሰዎቹም ይሔንን ሲያዩ ፣ እንዲህ ብለው ጮሁ ፣
“እግዚአብሔር አምላክ ነው፡፡” ኤልያስም እንዲህ አለ ፣
“የበአል ነብያትን ያዙአቸው፡፡ እንዲያመልጡም
ለአንዳቸውም አትፍቀዱላቸው፡፡” ኤልያስም ንጉሱ
አክዓብ ከብዙ ጊዜ በፊት ማድረግ የነበረበትን ነገር
አደረገ፡፡ ሐሰተኛ ነብያቱን ገደላቸው፡፡




የእግዚአብሔርም አገልጋይ
ለአክዓብ ዝናብ እየመጣ እንደሆነ
ነገረው። በፍጥነትም ፤ ታናሽ
ደመና ታየች ፤ ዝናብ ሊዘንብ ይሆን;
ከሶስት አመት አሰቃቂ ድርቅ በኋላ?



ከጥቂት ጊዜም በኋላ ፤ ሰማዩ
በደመናት እና በንፋስ ምክንያት
ጠቆረ ፤ ከዚያም ከባድ የሆነ
ዝናብን ጣለ። እግዚአብሔር
ዝናቡን ላከው። ኤልያስ
እውነትን እየተናገረ እንደነበረ
እግዚአብሔር አረጋገጠላቸው።



ንጉስ አክዓብ እግዚአብሔርንና
አገልጋዩን ኤልያስን
እንዳከበራቸው ታስባለህ;
በእርግጥ ፣ ኤልዛቤል ኤልያስን
ልትገድለው ሙከራ አድርጋለች
፤ ነገር ግን ሸሽቷል።
በስተመጨረሻም፣ አክዓብ
በጦር ሜዳ ሞተ እና
አገልጋዮቹ ኤልዛቤልን ከሰገነቱ
ጣሪያ ላይ ወርውረው ጣሏት።
ከድንጋይጋ ተላትማ ሞተች።



ኤልያስ ላይ ምን ተከሰተ; አንድ ቀን የእሳት
ሰረገላን ከእሳት ፈረሶችጋ አድርጎ
እግዚአብሔር ላከ። ኤልያስም ፤
የእግዚአብሔር የእሳት ልጅ ፤ ወደ ሰማይ
በፈጣን ንፋስ ተወሰደ።

የእሳት ሰው።

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

1ኛ ነገስት 17-19 ፤ 2ኛ ነገስት 21

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን ግሩም ስለሆነው አምላካችን
እግዚአብሔር እኛን በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር እንዳደረግን ያውቀዋል።
የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን
አንዱንና ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት እንዲከፍል አደረገው።
ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ!
ያላመንን እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል
ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል። እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤
እኛም በእርሱ ውስጥ ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት
ለመሞት ስትል ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባ
ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን ይኖረኛል አንድ ቀን
ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና
እንደ ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16